

# ክፉው በደግ ሲለወጥ

17-2

## ዮሴፍ ክፉው እንዴት በጎ ሆነለት?

1. አልማረከም አለ
   የሚያገጥመውን ፈተና ፊት ለፊት በመጋጠም ፈንታ "ተሸንፌአለሁ" ብሎ አላቆመም። እርግጥ ነው ያጋጠመው ትልቅ ፈተና ነበር። ባርያ ሆኖ ሲሸጥ በውስጡ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ሊፈጠርበት ይችላል። "ትክክለኛና ንጹሕ የሆነ ሕይወት ለመኖር ሞክርያለሁ። በሕይወቴም አግባብ ባለው ሁኔታ ተራምጃለሁ፤ ግን ያጋጠመኝ ሁኔታ ምንድነው? እነሆኝ ባርያ ሆኜ በግብጽ ውስጥ አገለግላለሁ፤" ለማለት ይችል ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ እራሱን ከጶጢፋር ቤተ ውስጥ አገኘ። በዚያም ፈተናው ስለአላባራለት እንዲህ ማለት ይችል ነበር። "ታዲያ ንጹሕና ትክክለኛ ሰው ሆኖ መኖር ለምን ይጠቅማል? ለምን ቀላሉንና አቋራጩን መንገድ አልወሰደም" ማለት ይችል ነበር። ይሁን እንጂ፥ ምንም እንኳን ሰዎች የጠሉትና የጎዱት እግዚአብሔርም የረሳው ቢመስልም፥ የዮሴፍ ክፉ ከመሆን ደግ፣ እምነት ከማጉደል ታማኝ፣ ከመርከስ ንጹሕ ሆኖ መኖር እንደሚሻል አመነ። በጥርጣሬ ቢሰቃይም እስከሚችለው ድረስ ታማኝ ሆኖ ለመኖር ሞከረ። በክፉ ጊዜ ያጋጠመውን ፈተና ታገለ እንጂ "ተሸንፍያለሁ" ብሎ እጁን አጣምሮ አልተቀመጠም።

2. የጥላቻ መንፈስ አላሸነፈውም
   ዮሴፍ መራራነት ወደ ነፍሱ እንዲገባ እድል ፈንታ አልሰጠውም። ጥላቻን ከሕይወቱ ለማስወገድ ምን ያህል ትግል አድርጎ ይሆን? ወንድሞቹ በጥላቻ ተሞልተው እንደዚያ ሲያንገላቱን፣ ሲደበድቡት፣ ከጉድጓድ ላይ ሲጥሉት፣ ከዚያም ወስደው ሲሸጡት፣ ከፍተኛ ጥላቻና መራራነት በውስጡ ስለ ወንድሞቹ ሊሰማው በተገባ ነበር። ዮሴፍ ግን ጥላቻ በሕይወቱ ውስጥ፥ በቀል በልቡ ውስጥ እንዲኖር አልፈቀደም። ዮሴፍ የግብጽ ጠቅላይ ሚኒስቴር በሆነበት ጊዜና ወንድሞቹም በእግሩ ሥር ተምበርክከው በሰገዱለት ጊዜ፥ ማንነታቸውን አውቆ በንዴትና በቁጣ ተሞልቶ "ያኔ እንዳትጎዱኝ ስለምናችሁ እምቢ ለምን አላችሁኝ? ጥያቄዬን ለምን አልተቀበላችሁም? እርግጥ ነው ልትጠሉኝ የቻላችሁበት አንዳንድ ምክንያት ይኖራችሁ ይሆናል። ይሁን እንጂ ልጅ ነው ሕጻን ነው ብላችሁ አልተዋችሁኝም፤ አዝናችሁና ራርታችሁ ከአደጋ እንዳመልጥ አላደረጋችሁኝም። አዎን! ትላንትና የእናንተ ነበር፥ ዛሬ ግን የእኔ ነውና እበቀላችኋለሁ" አላላቸውም። ዮሴፍ በልቡ ውስጥ ጥላቻ በቅሎና ሥር ሰዶ ሕይወቱን እንዲቆጣጠረው አልፈቀደም። ነገር ግን በይቅርታና በፍቅር ተሞላ። "ወንድሞቼ እኔን ሊያጠፉኝ እንደ ሞከሩ እኔም እንደክፋታቸው አጸፋውን እመልስላችኋለሁ" አጠፋችኋለሁ ብሎ አልተበቀለም። ዮሴፍ በቀልን በእጁ አልወሰደም "በቀል የእኔ ነው" የሚለውን የእግዚአብሔርን ሥፍራና ቦታ ለመያዝ አልሞከረም።

ዮሴፍ ይህንን ከፍተኛ ትምህርት በሕይወቱ ተምሯል። ዮሴፍ በጥላቻና በቀልን ከሕይወቱ ያስወገደ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ደግሞ ይቅር ማለትንም ተምሯል። ይቅር ማለት በመቻሉም ለብዙ ሰዎች

ደህንነት መሆን ቻለ። ለወንድሞቹና ለአባቱ የደህንነት ምክንያት ሆነ፤ እንዲሁም ለዓለም ሁሉ በረከት ሆነ። እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ስለሆነ፥ በጥላቻ የተሞላ ሰው ከእርሱ ጋር ኅብረትና አንድነት አይኖረውም። እግዚአብሔርን እወዳለሁ ብሎ ወንድሙን የሚጠላ ቢኖር እርሱ ውሸታም ነው። ይህንን ሃሳብ ሐዋርያው ዮሐንስ በመልዕክቱ ጽፎታል። ዮሴፍ የፍቅርና የይቅርታ ልብ ባይኖረው ኖሮ፥ ክፉውን ነገር ወደ በጎ እግዚአብሔር ጨርሶ ሊለውጥለት ባልቻለም ነበር። እግዚአብሔር የሚተባበረው በፍቅር የተሞላውን እንጂ፥ በጥላቻ የተሞላውን ሰው አይደለም። ዮሴፍ የወንድሞቹን ክፉ ሥራ በመዝለል "ምንም አላደረጋችሁም፤ ደግ ነው" አላላቸውም። "እንደዚያ ልታደርጉብኝ የቻላችሁት በቂ ምክንያት ስለነበራችሁ ነው። ደግሞም ልትጎዱኝ ብላችሁ አልነበረም" ብሎ አላላቸውም። ግን እውነቱን ፊት ለፊት ነገራቸው። "እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፥ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው" (ዘፍ. 50፥20) አላቸው። "የእናንተ ፍላጎትና ሃሳብ በእኔ ላይ ክፉ ለማድረግ እንደነበረ ግልጽ ነበር፤ ግን እግዚአብሔር ለበጎ አደረገው" ብሎ ተናገራቸው። ልታጠፉኝ ነበር ዛሬ ለመዳን የቻልኩት ወይም በሕይወት የምመላለሰው በእናንተ ፍቅር ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድና ጸጋ ነው" ሲል እውነቱን ነገራቸው።

ታዲያ ዮሴፍ እንዴት ይቅር ሊላቸው ቻለ?

1) የስቃዩ ምክንያት ወንድሞቹ እንደሆኑና ኃላፊነትም እንደነበረባቸው ነገራቸው። እነርሱ ባጠፉት እግዚአብሔርን መውቀስ አልፈለገም። ብዙ ጊዜ ሰዎች በሕይወታቸው የማይፈልጉትን ነገር ወይም በጎ ያሆነ ነገር ሲያጋጥማቸው፥ የዚያ ነገር ምክንያት የሆነውን ሁኔታ ወይንም ሰው በመውቀስ ፈንታ እግዚአብሔር እንዳደረሰባቸው አድርገው የሚናገሩ ሰዎች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ጌታን እናውቃለን ክርስቲያን ነን በሚሉ አንዳንድ ሰዎች ጉዳት ሲደርስባቸው፥ ሲያስቀይሟቸው፥ ክርስቲያኖችን በአጠቃላይ የሚጠሉ ከክርስቲያኖች ሁሉ የሚሸሹ ሰዎች አሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን ከቤተክርስትያን የሚርቁ፥ ከእግዚአብሔር የሚሸሹና በእግዚአብሔርም ላይ ቅያሜ የሚያሳዩ ሰዎች አሉ። ይሄ በመሠረቱ ትክክል አይደለም። ዮሴፍ ወንድሞቹ ባጠፉት ምክንያት እግዚአብሔርን እንደ ጥፋተኛ አድርጎ መቁጠር አልፈለገም።

2) ዮሴፍ የተረዳው እግዚአብሔር የዚህ ክፉ ሁኔታ አመንጪ ምክንያት እንዳልሆነ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ ክፉውን ነገር እግዚአብሔር እንደለወጠው ተረዳ። "እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ለመልካም አሰበው" አለ። "እግዚአብሔር በእኔ ወገን ነበር። እርሱም ስለረዳኝ መጥፎ ሊሆን የሚችለው ነገር በእርሱ ኃይል በጎ እንዲሆንልኝ ሆነ። የእርሱ እርዳታ በሕይወቴ ስላልተለየኝ ጨለማ ውና የጨፈገገው ሁኔታ ተለውጦ ብርሃን በራልኝ። በጨለማ ውስጥ ባልፍ እንኳን በእርሱ ስለተማመ ንኩ የተስፋ ብርሃኑን አፈነጠቀልኝ። እርሱ ስለረዳኝ ዛሬ መሆን የምችለውን መሆን ቻልኩ። ሊያጠፉኝ የመጣው ክፉ ሁኔታ ለበጎ ሆነልኝ። እኔ ብርቱና ደፋር ስለሆንኩ ሳይሆን እግዚአብሔር በእኔ በኩል ሆኖ ስለሠራልኝና ስለአገዘኝ ነው" አለ።

የእግዚአብሔርን አስደናቂና እንዲሁም ከፍተኛ ፍቅር ሲመለከት በልቡ ውስጥ ፍቅር እንጂ ጥላቻ ስፍራ ሊኖረው አልቻለም። ጥላቻን አስወግዶ በሕይወቱ ፍቅር እንዲሞላው ሊሆን የቻለው መጥፎን ሁኔታ የለወጠለት የእግዚአብሔር በጎና ቸርነት በሕይወቱ በዝቶ ስላየው ነው። ከዚህም ሌላ ደግሞ በፍቅር የተሞላው እግዚአብሔር የእነዚያ የጥፋተኞችና የበደለኞችም አባት እንደሆነ ስላወቀ ነው። በደሎኞችና ኃጢአተኞችም የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆኑ፥ ያ በጎ ያደርገለትን አምላክ ሊያሳዝነው አልፈለገም። በዚህ ምክንያት ዮሴፍ የበደሉትን ወንድሞቹን ይቅር ማለት ቻለ። ይቅር በማለቱም በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለመሆን ቻለ። በዚህም ምክንያት ክፉው ነገር ወደ በጎ ተለወጠለት። የእኛም ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም። "እግዚአብሔርን ለሚወዱ እንደ ሃሳቡም ለተጠሩ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው' ይላል።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**